የአውሮፓና የአፍሪካ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች ምክር ቤት
The Council of European and African Kinijit Support Groups
1 Crowndale Road London NW1 1TU UK Tel: +44 (0) 20 7168 9893 Email: euafkinijit@googlemail.com

**በቅንጅት አመራር ዉስጥ የተፈጠረዉን ዉዝግብ አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ!!**

በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት የልዑካን ቡድን ከፍተኛ አመራር ዉስጥ የተነሳዉ ዉዝግብ በኢትዮጵያ ሕዝብ በፓርቲዉ አባላትና ደጋፊዎች ዘንድ ከፍተኛ ሐዘንና ግራ መጋባት ፈጥሯል:: ዉዝግቡ በቀላሉ ሊፈታ የሚችል መሆኑ በተደጋጋሚ የተገለጸ ቢሆንም፣ አለመግባባቱ ተወግዶ መሪዎቹ በአንድ ላይ ተግባራቸዉን ሲያከናዉኑ አለመታየታቸዉ የቅንጅትን አርማ አንግበዉ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙትን ወገኖች ሁሉ ይበልጥ እያሳሰበና እያስቆጣ ነዉ::

መቻቻልን፣ ፍቅርን፣ አንድነትንና ሰላምን የትግሉ አስኳል አድርጎ በመንቀሳቀስ ላይ በሚገኘዉ የቅንጅት አመራር አባላት መካከል ዉዝግብ መከሰቱ አሳዛኝ ድርጊት ነዉ:: ቁርሾዉ ፓርቲዉ ይዞት በተነሳዉ የዴሞክራሲ፣ የፍትህ፣ የአንድነት፣የነጻነትና የእኩልነት ጥያቄ ዙሪያ ግልጽ የሆነ ርዕዮተዓለማዊና ፓለቲካዊ ልዩነት ሳይኖር መሆኑ ግራ የሚያጋባ ነዉ:: ከዚህም ሌላ የሕዝብን ድምጽና መብት አሳልፈን አንሰጥም በማለት በአንድነት በጽናት ቆመዉ ከፍተኛ መስዋዕትነት በከፈሉና በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ተወዳጅነትና ከበሬታ ባተረፉ፣ ባለራዕይ የሕዝብ መሪዎች መከከል መሆኑ ትልቅ አንቆቅልሽ ሆኖ ይታያል:

ቅራኔ፣ግጭትና አለመግባባት በማንኛዉም ሰብሰብ ዉስጥ የነበረ፣ ያለና የሚኖር ማህበራዊ ክስተት ነዉ:: በቅንጅትም ዉስጥ ተመሳሳይ ችግር ሊፈጠር መቻሉ አያስደንቅም ሊባል ቢችልም፣ ችግሩ በድርጅቱ የዉስጥ ደንብና መመሪያ መሰረት መፈታት ይገባዉ የነበረ አለመግባባት ወደ አደባባይ ወጥቶ የጠላት መሳለቂያ፣ ድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ደግሞ የህሊና ቁስል መሆን አይገባዉም:: «ከደፈረሰ ዉሃ ዓሳ ማጥመድ» የለመዱና የሚፈልጉ አፍራሽ ሃይሎች ዉዝግቡን በማራገብ በቅንጅት ኪሳራ የፓለቲካ ትርፍ ለማግኘት በመገናኛ ብዙሃን ዙሪያ ሳይቀር አሽምቀዉ የወሬ አሉባልታ በማራገብ ቅራኔዉ ይበልጥ አንዲካረርና የድርጅቱ አንድነት እንዲናጋ ደፋ ቀና ሲሉ ማየት የጋለ ብረት እንደ መጨበጥ ይቆጠራል::

አብረዉ የሚሰሩ ሰዎች በሐሳብ መለያየታቸዉ፣ወይም አለመግባባቶች ይፈጠራሉ:: ጊዜ፣ቦታና ወቅት በሰዎች አመለካከትና አሰራር ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ ወይም ልዩነት መፈጠሩ ሊያስደንቅ ወይም አዲስ ሊሆን አይችልም:: ዋናዉ ቁም ነገር በቅራኔ አያያዙና አፈታቱ ላይ ያለዉ ጥበብ ወይም ዘዴ ላይ ነዉ:: ታዲያ እንደ ቅንጅት ያለ የአገርን ምስቅልቅል የፓለቲካ ችግር በሰላማዊና ሕጋዉ መንገድ ለመፍታት የሚንቀሳቀስ ድርጅት በመሰረታዊ ቅራኔ ላይ ያልተመሰረተን ዉስጣዊ ችግር ለመፍታት ያቅተዋል ብሎ ማሰብ አይቻልም:: ስለሆነም ይህ ሁኔታ ተለዉጦ በሕዝብ ደምና መስዋዕትነት የተገነባዉ የቅንጅት ለአንድነትና ፓርቲ አንድነቱ ተጠብቆ እንቅስቃሴዉን እንዲቀጥል መሪዎች፣አባላትና ደጋፊዎች የተሸከሙት ሕዝባዊ አደራ ለመወጣት የተለመደ ቆራጥ ትግላቸዉን ማድረግ ይጠብቅባቸዋል:: ዉይይትና ድርድርን የቅራኔ መፍቻ ቁልፍ አድርጎ ለሚንቀሳቀሰዉ ቅንጅት የዉስጥ ችገሩን በሰለጠነ መንገድ እንዲፈታ ለዴሞክራሲ፣ ለፍትህና ለነጻነት የቆሙ ወገኖች ሁሉ ሊያበራታቱትና ድጋፋቸዉን ሊሠጡት ይገባል:::

የአዉሮፓና የአፍሪካ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ካዉንስል በፓርቲዉ አመራር ዉስጥ የተፈጠረዉ ችግር በወቅቱ ካልፈታ በእንቅሰቃሴዉ ላይ ብቻ ሳይሆን በድርጅቱ ህልዉናና በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ትግል ሂደት ላይ አሉታዊ አንድምታ እንዳያስከትል ስጋት አለዉ:: ስለሆነም አለመግባባቱ በአፈጣኝ ተፈትቶ ፓርቲዉ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ላይ አስተዋጽኦ የሚመለከታቸዉ ወገኖች ሁሉ አስፈላጊዉን ጥረት እንዲያደርጉ የሚከተለዉን ጥሪ ያስተላልፋል::

1. ቅንጅትን ቅንጅት ያደረገዉና በሕዝብ ልብ እንዲሰርጽ ያደረገዉ ህብረ-ብሄራዊነቱ፣ ዴሞክራሲያዊነቱ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት አራማጅነቱ፣ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ያለዉ አቋም ነዉ:: ስለሆነም ሁሉም ወገኖች በአመራሩ ዉስጥ የተፈጠረዉ ችግር መፍታት እንዳለበት ተገንዝበዉ ችግሩን በጠረጴዛ ዙሪያ ዉይይት እንዲፈቱ እንጠይቃለን::

2. ብዙ መስዋዕትነት የተከፈለበትንና የኢትዮጵያ ሕዝብ የነጻነትና የዴሞክራሲ ፈር ቀዳጅ አድርጎ የሚመለከተዉን የቅንጅትን ፓርቲ በየትኛዉም ወገን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ለግላዊም ሆነ ለቡድናዊ ጥቅም ሲባል የሚደረገዉን የመከፋፈል፣ብሎም የማደከም ሙከራ በጥብቅ እንቃወማለን::

3. የመገናኛ ብዙሃን በሐቅ ላይ የተመሰረተ መረጃና ዜና ለሕዝብ የማሰጨራት ያላቸዉ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንዳንድ የሜዲያ አዉታሮች (ሬዲዮኖች፣ፓልቶክና ድረገጾች) በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በቅንጅት ድርጅታዊ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የሚያራምዱት ወገናዊነት የሚታይበት አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ የድርጅቱን አንድነት እንዲላላ በማድረግ ላይ መሆኑን ተገንዝበዉ ትክክለኛ መረጃ በመስጠቱ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ጥሪያችንን እናቀርባለን::

4. የቅንጅት መሪዎችና አባላት በሜዲያ ላይ መግለጫ የሚሰጡት እርስ በርሱ የሚጋጭ መግለጫ ድርጅቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያለዉን ትክክለኛ ፓሊሲና አቋም ለማወቅ ግራ አጋብቶአል:: በአመራሩ መካከል የሚታየዉንም አለመግባባት አያጋጋለዉ ነዉ:: በመሆኑም በዘፈቀደ የሚደረግ አሰራር የድርጅቱን ስም አንዳያጎድፍ የሚያወጡ መግለጨዎችና የሚሰጡ ቃለመጠይቆች ድርጅቱ ሃላፊነቱን በሚሰጣቸዉ ሰዎች አማካኝነት ብቻ እንዲደረግ አስቸኳይ የእርምት እርምጃ እንዲወስድ እናሳስባለን::

5. ከሁሉም በላይ ደግሞ ክፉዉንና ደጉን በጋራ ያዩ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ አመኔታና ከበሬታ ያገኙት የቅንጅት መሪዎች በመካከላቸዉ የተፈጠረዉን አለመግባባት በዉይይት በመፍታት አንድነታቸዉን አጠንክረዉ የተጀመረዉን የዴሞክራሲ ትግል አስተባብሮ የመምራቱን ሃላፊነት እንዲቀጥሉ ሕይወታቸዉን ለመስዋዕትነት በሰጡ ወገኖቻችን ስም እንማጸናለን::

6. የቅንጅት አንድነት ሳይናጋ የተፈጠረዉ አለመግባባት ተወግዶ፣ የፓርቲዉ አንድነትና ህልዉና ተረጋግጦ፣የህዝብ የትግል ስሜት ተጠብቆ ድርጅቱ ያነገባቸዉ እሴቶች ሳይደበዝዙ የተጀመረዉ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የነጻነት ትግል ተጠናክሮ እንዲቀጥል መላዉ የቅንጅት ቤተሰቦችና የኢትዮጵያ ሕዝብ ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን::

ቅንጅት አንድ ነዉ!!

ኦክቶበር 2007

1 Crowndale Road London NW1 1TU UK Tel: +44 (0) 20 7168 9893 Email: euafkinijit@googlemail.com